# የተመረጡ ፍርዶች

(በቤተሰብ ህግ ላይ ያተኮሩ)

የሰ/መ/ቁ. 43988

መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰኒያ ሼኅ ተማም - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ በላይነሽ ማቴቦ

2. አቶ ሽሪፊ አህመድ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ ወንድ ከሁለት ሴቶች ጋር ጋብቻ ፈጽሞ ሲኖር ከቆየ በሁዋላ ከአንደኛዋ ጋር በፍቺ ሲለይ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚያስተናግድበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክር የተጀመረው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ለጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ ፍርድ ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ይዘት ባጭሩ ሲታይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሲኖሩ በእንሲኖ ከተማ ውስጥ አንድ ክፍል ቆርቆሮ ቤት ማፍራታቸውንና የገጠር መሬት አራት ጥማድ የነበራቸው መሆኑን ገልፀው እነዚህን ንብረቶች 2ኛ ተጠሪ እንዲያካፍላቸ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሠጡት መልስም 1ኛ ተጠሪ ጋር የተጋቡት በ1998 ዓ.ም ሆኖ እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ቆይታ መሄዷንና በ1994 ዓ.ም ሌላ ጋብቻ አለኝ በማለቷ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ፈጽማ የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ መወሰኑን በጋራ ያፈሩት ንብረት አለመኖሩን ንብረቶቹ የተፈሩት ከአሁኗ አመልካች ጋር መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አመልካች ወደ ክርክሩ በጣልቃ ገብነት ለመግባት ማመልከቻ አቅርበውና የስር ፍርድ ቤት ፈቅዶላቸው ባቀረቡት ክርክር ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ ፈጽመው ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ያፈሩት አመልካች እንጂ የአሁኗ 1ኛ

ተጠሪ ያለመሆናቸውን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የገጠር

መሬትን በተመለከተ የጋራ ባለሀብቶች የአሁኗ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ መሆናቸውን የቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ ግን የጋራ ባለሀብቶች ተጠሪዎች ስለሆኑ እኩል ሊካፈሉ የሚገባቸው መሆኑን ገልፆ ወስኗል፡፡ በዚሁ የቆርቆሮ ቤቱን በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል አመልካች ቅር በመሰኘት በየደረጃው ላሉት ፍ/ቤቶች ይግባኝና የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሕጋዊ ጋብቻ በ1980 ዓ.ም በመመስረት አከራካሪውን ቤት ስለማፍራታቸው ማስረጃ አቅረበውና አረጋግጠው ባለበት ሁኔታ ንብረቱ የተጠሪዎቹ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የአመልካችና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ በእንሲኖ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት የተሰራ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ እንዳለ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሣያል፡፡ ስለሆነም ቤቱ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጋብቻ ፀንቶ እያለ የተሰራ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ንብረቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 30 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በመገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካችና የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ሕጋዊ ጋብቻ በ1980 ዓ.ም መሥርተው እስካሁንም አንድ ላይ ያሉ መሆኑን፣ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ከአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ጋር በ1988 ዓ.ም ጋብቻ መስርተው እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ከኖሩ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ጥላው በመሄድ በሌላ ቦታ ቆይተው በ 1994 ዓ.ም የፍች ጥያቄ አቅርበው መለያየታቸውን፣ በእንሴኖ ከተማ ውስጥ ይገኛል በተባለው ቦታ ቀድሞውንም የሳር ቤት የነበረና ይህ ቤት ፈርሶ 2ኛ ተጠሪና አመልካች አንድ ላይ ሆነው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት መስራታቸው በማስረጃ መረጋገጡን፣ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት አይገባቸውም በማለት ሊወስን የቻለው ቤቱ የተሰራበትን ቦታ የያዙበትን መንገድና መቼ እንደያዙ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ መብት

የሌላቸው መሆኑን አላስረዱም፣ ንብረቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ስለማድረጋቸውም የሚያሳይና በፍርድ ቤት የተመዘገበ የፅሑፍ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ከሣሽ ክስ ሊመሰረትበት የሚገባው ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ለክሱ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ከሣሹ መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ የከሣሽ እንጂ የተከሳሽ ሊሆን አይገባም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት መብት የላቸውም ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች የተወሰነው 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት የሌላቸው ስለመሆኑ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ምስክሮች አልተመሰከረም በሚል ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ቤቱ የተሰራው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በጋብቻ ፀንተው በነበሩበት ጊዜ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ሲሆን የአመልካችን ክርክር ውድቅ ሊያደርግ የቻለው ቦታው በምን መልኩ እንደተያዘና መቼ እንደተያዘ እንዲሁም ቤቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የጋራ ስለመደረጉ በፍርድ ቤት የተመዘገበ ማስረጃ  አላቀረቡም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባዶ ቦታ ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝቦች ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገመንግስትና በሌሎች አግባብነት ባለቸው ሕጎች የተረጋገጠ ሲሆን አንድ ሰው በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት በህጉ አግባብ በተሠጠው የባለይዞታነት መብት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው በተገቢው መንገድ ባለይዞታነቱን ሲያረጋግጥ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ የነበራቸው ስለመሆኑ በስር ፍር ቤት የተረጋገጠ ሲሆን አከራካሪው ንብረት ግን በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ የተሰራ እንጂ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ የተሰራ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም ጋብቻቸውን በ1990 ዓ.ም ትተው መሄዳቸውንና አከራካሪው ቤትም በዚሁ ወቅት ስለመሰራቱ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ጋብቻቸውን በተገቢው መንገድ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያፈረሱት በ1994 ዓ.ም ቢሆንም ለአከራካሪው ቤት መሰራት ግን ያደረጉት አስተዋጽኦ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ በእርግጥ ጋብቻው በሕጉ አግባብ ሣይፈርስ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ስለመሆኑ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ነጥብ ነው፡፡ ሆኖም ጋብቻው በተገቢው መንገድ ሣይፈርስ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት ሌላው ተጋቢ ያፈራውን ንብረት የጋብቻ ውጤት  ነው በማለት የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ንብረቱ የጋራ ነው የሚለውን የሕግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆን አይገባም፡፡ ለንብረቱ መፈራት ምክንያት የሆነው ተጋቢ የንብረቱ የግል ባለህበት ይሆናል እንጂ ምንም አስተዋጽኦ

ያላደረገ ተጋቢ እንዲካፈል ማድረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ ስር የተቀመጠውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚጥስና የህግ መሠረት የሌለው ነው፡፡ የቤተሰብ ሕጉ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ንብረት የጋራ ነው የሚል ሕጋዊ ግምት የወሰደውም ተጋቢዎች ለንብረቱ መፍራት የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ታሣቢ በማድረግ ነው ተብሎም ይገመታል፡፡ ይህ ግምት ግን በተቃራኒ ማስረጃ የማይስተባበልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ጋብቻ በሕጉ አግባብ ሣይፍርስ አንደኛው ተጋቢ ጋብቻውን ትቶ በሄደበት ወቅት ቀሪው ተጋቢ ሌላ ሰው አግብቶ ንብረቱን ማፍራቱ በሚገባ እስከተረጋገጠ ድረስ ጋብቻውን ትቶ የሄደ ተጋቢ በሌላ ጊዜ በመምጣት በሌለበት የተፈራውን ንብረት ልካፍል በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ በሕገ መንግስቱ ስለንብረት ማፍራት መብት የተደረገውን ጥያቄ እና በቤተሰብ ሕጉም ስለባልና ሚስት የጋራ ንብረት የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሠረት ያደረገ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች አከራካሪውን ንብረት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ሁኖ እያለ ድርሻ የላቸውም የተባለው ያላግባብ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የበታች ፍርድ ቤቶች በእንሴኖ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቆርቆሮ ቤት እኩል ሊካፈሉ የሚገባቸው ተጠሪዎች ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር እኩል መብት ያላቸው አመልካች እንጂ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ (ወ/ሮ በላይነሽ ማተቦ) አይደሉም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 67924

መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡-ሓጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ምንያ ገ/ስላሴ - አልቀረቡም

**ተጠሪዎች**፡- ወ/ሪት መሠረት ዓለማየሁ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምረ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው በጋብቻ ተሳስረው የነበሩት ተጋቢዎች ለረዥም ጊዜ ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ይህ የትዳር ግንኙነት ተቋርጧል የሚባለው እንዴት ነው? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ አስመልክቶ የአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ የህግ ጥያቄ አስመልክቶ ከሰጠው ትርጉም ጋር በማገናዘብ አግባብነቱን ለመመልከት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚስትነታቸውን የሚያረጋግጥ ውሳኔ ካገኙ በኋላ የአሁን ተጠሪ የሟች ልጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት ይኸው ውሳኔ መብታቸውን እንደሚነካ በማስረዳት የክርክር ተካፋይ ከሆኑ በኃላ አመልካችና ሟች አባቴ በህግ በታወቀ የጋብቻ ሥርዓት ግንኙነት አልመሰረቱም፤ ጋብቻ አለ እንኳ ቢባል አመልካች ከአስር ዓመታት በላይ ኑሯቸውን ውጭ አገር አድርገው ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ ጋብቻው ፈራሽ ነው፡፡ በመሆኑም የተሠጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን እንደገና አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ በአመልካችና በሟች መካካል የጋብቻ ግንኙነት ስለመኖሩ በሁኔታ ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳን አመልካችና ሟች ጋብቻቸው ባለበት ጊዜ በተለያየ ሀገር ተለያይተው መኖራቸው ቢታወቅም ጋብቻቸውን ቀሪ አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ አንቀጽ 55 እንደተመለከተው ተጋቢዎች በስምምነት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰ ጊዜ ተለያይተው መኖር እንደሚችሉና

መብታቸው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የሟች ሚስት ናቸው በማለት የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሳኔ ሊሰረዝ የሚችል አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የአ/አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአሁን አመልካችና ሟች የጋብቻ ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ተቀብሎ፤ ነገር ግን ሁለቱም ለ18 ዓመታት ያህል ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት የቀጠለ የትዳር ግንኙነት እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 31891 ለረዥም ጊዜ ተለያይተው ከኖሩ፤ በዚህም ጊዜ ውስጥ የባልና ሚስት ዓይነት ግንኙነት ያልነበራቸው ሰዎች ሚስትነት ወይም ባልነት ተረጋግጦ ማስረጃ ሊሰጣቸው እንደማይችል ያመለከተ ሲሆን በሌሎች የሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቦችም ተመሳሳይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ሟችና የአሁን አመልካች ለ18 ዓመት ተለያይተው የኖሩና በዚህም ጊዜ ውስጥ የትዳር ግንኙነታቸው ባቋረጡበት ሁኔታ የአሁን አመልካች ሚስት ናቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ሆኖ አልተገኘም በሚለው ትችት መነሻ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ የአ/አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይኸው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም በማለት የአሁኑ ተጠሪን አስቀርቦ ሳያከራክር መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ይህን ሲመስል ግራ ቀኙ ከዚህ ቀደም በስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር በሰበር ደረጃ የፁሁፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካችና የተጠሪ አባት ሟች የጋብቻ ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤቶች በተሠጡት ዳኝነቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው ይህ የጋብቻ ግንኙነታቸው ሁለቱም ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ተቋረጧል ወይም  አልተቋረጠም በሚለው ጭብጥ ስር የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው እና የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አከራካሪ ነጥብ ስር በሌሎች ወገኖች ክርክር መነሻ የሰጠውን ትርጉም መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

የአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ምንም እንኳ የአሁን አመልካችና ሟች በተለያየ ሀገር በመኖራቸው በኑሮ የተለያዩ ቢሆኑም የጋብቻ ግንኙነታቸው ግን ሳይቋረጥ የዘለቀ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ውሳኔ የሰጠው በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡትን የሰው እና የተለያዩ የሰነድና ገላጭ ማስረጃዎችን መሰረት በማደረግ ነው፡፡ በአኳያው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የነበረው የጋብቻ ግንኙነት መቋረጡን አረጋግጫለሁ ያለው በአመልካች በኩል በቀረበው የሰነድ እና ገላጭ ማስረጃዎች ሆኖ የቀረበውን በቪዲዮ የተቀረፀውን ምስል ብቻ ምርኩዝ አድርጎ የማስረዳት ብቃቱን በመመዘን እንደሆነ የውሰኔው ግልባጭ አስረጂ ነው፡፡ ይኸውም የሥር

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርቦ ከተመለከተውና ለውሳኔው መነሻ አድርጎ ከያዘው ማስረጃ መካከል በአመልካች አማካኝነት የቀረቡት የደብዳቤ ልውውጦችና ፎቶግራፎች ተጠሪዋ የአሁን አመልካች በውጭ ሀገር በነበረችበት ጊዜ ከሟች ጋር የነበራት ግንኙነት አለመቋረጡን ያመለክታል፤ የወረዳ 19 መረዳጃ እድር የቀረበው መግለጫ ሟች እና የአሁን አመልካች በባልና ሚስት መመዝገባቸውን አረጋግጦ በመላኩ የቀረበውም የቪዲዮ ፊልም የአሁን አመልካች ከውጭ ሀገር ለሟች በምትልከው ገንዘብ ሟች ቤቱን እየሰሩ መሆኑን በማረጋገጥ የደረሰበትን ውጤት ለባለቤታቸው ለአሁ አመልካች ለመግለፅ መልዕክቱን ለመላክ የተቀረፀ ሲሆን ከዚሁ ምስል ሟች ከአሁን አመልካች ጋር የትዳር ግንኙነትታቸው ያልተቋረጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል በሚል የማስረጃውን አግባብነትና ሚዛን የመረመረበትን ክፍል ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዕድር የመጣው ማስረጃ የዕድሩ ማህተምም ሆነ ቁጥር የሌለው በመሆኑ ተአማኒነት ያለው ነው ብሎ ለመቀበል የሚቻልበት አይደለም፤ የግል ደብዳቤዎችና ፍ/ቤቱ የተመለከተው የቪዲዮ ማስረጃ የትዳር ግንኙነት ስለመቀጠሉ የሚያመለክት ነገር የሌላቸውና እምነት የሚጣልባቸው ማስረጃዎች አይደሉም፡፡ ለሟች 40 ቀን መታሰቢያ የታተመው የጥሪ ወረቀትም በማንኛውም ጊዜ ሊታተም የሚችል በመሆኑ ታማኝነት ያለው አይደለም የሚለውን ትችት በመስጠት ከጋብቻ የመነጨው ግንኙነት ስለመቀጠሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

በእርግጥ ይህ በፍሬ ነገርና ፍሬ ነገርን ለማስረዳት የቀረበውን ማስረጃ ታማኝነት የመመርመርና የማስረዳት አቅሙን የመመዘን ሥልጣኑ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንጂ ለዚሁ የሰበር ችሎት በህግ የተሰጠው ሥልጣል ባለመሆኑ በዚህ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በማስረጃ አመዛዘን ረገድ የሰጠውን ዳኝነት እንደገና ለመመርመርና አግባብነቱን ለማየት የሚቻል አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ በአሁን አመልካችና በሟች መካከል የነበረውን የጋብቻ ግንኙነት በመኖሪያ ቦታ መለያየት የተነሳ ሳይቋረጥ ግንኙነት እንዳለ እንደቀጠለ ነበር በማለት የአሁን አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ እና የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ለሰጠው ውሳኔ ምርኩዝ አድርጎ የያዘው ማስረጃ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ትችት ባሳረፈበት የሰነድ እና ገላጭ ማስረጃዎች ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ የሟች እህት የሆኑትን እና የሟች ጐረቤትን የምስክርነት ቃል ሁሉ የያዘ ነው፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የምስክርነት ቃል ውስጥ ሁለቱም በአካባቢው በእድር፣ እና በቤት ስራ ማህበር በባልና ሚስትነት እንደሚታወቁ፤ ሟች ሥራ ስላልነበራቸው ተጠሪዋ የቤተሰባቸውን ኑሮ ለመለወጥ ከባለቤታቸው ጋር ባደረጉት ስምምነት ወደ ውጭ አገር ሄደው ሥራ በመስራት በሚልኩት ገንዘብ ቤት መስራታቸውን፣ ሟችም ሲታመም ገንዘብ በመላክ ታስታምመው

እንደነበር፣ እስከ ሟች ዕለተ-ሞት በትዳር ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ በመግለጽ ያረጋገጡበት ይገኙበታል፡፡
ስለዚህ የሰው ማስረጃ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያለው የለም፡፡ ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ከማስረጃው አግባብነት፣ ተቀባይነት እና የማሳመን ብቃት አንጻር በማየት የማይቀበለው ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሳይመለከተው የቀረ ካልሆነ በቀር ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን የተከራካሪ ወገን ማስረጃ በዘፈቀደ ውድቅ ማድረግ እንደማይቻል ስለማስረጃ አቀባባል በተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 257 ፣ 258 እና 259 ተመልክቷል፡፡ ይህም የተከራካሪ ወገንን የመደመጥ መብት ለማስከበር ሲባል የተዘረጋ ሥርዓት ነው፡፡ እንዲሁም የበታች ፍ/ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤ የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መሥጠት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 በተመለከተው የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት ተደንግጓል፡፡ የበላይ ፍርድ ቤትም ይህ ዳኝነት የፍርድ አፃፃፍ ስህተት የማስረጃ አቀባበል ስርዓት ጉድለት መፈፀሙን የሥር ፍ/ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ የሚያስረዳና ሳይመረመርና ሳይታይ የታለፈው የማስረጃ ይዘት በመዝገቡ ላይ ሰፍሮ ከተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.242 መሰረት በዚሁ የመዝገብ ግልባጭ ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊውን ዳኝነት መስጠት እንደሚቻልም ተመልክቷል፡፡
ስለሆነም የአሁን አመልካችና የሟች የጋብቻ ግንኙነት ሳይቋረጥ እስከ ሟች ዕለተ ሞት ድረስ ግንኙነት የቀጠለ ስለመሆኑ የሥር የአ/አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰው ማስረጃ ያረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ይህም ከሆነ በሀገሪቱ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎምና አፈጻጸም ማስፈን ይቻል ዘንድ እንደ አንድ ስልት ተቆጥሮ በወጣው በአዋጅ ቁጥር 454/97 ድንጋጌ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው የሰጡት የህግ ትርጉም በበታች ፍ/ቤቶች የአስገዳጅነት ኃይል ወይም ባህርይ የሚኖረው ትርጉም በተሰጠበት የተነሳው እና ዳኝነት እንዲሰጥበት በቀረበው ጉዳዮች መካከል የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የተመሳሰለ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡
ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት የተጠቀሰውንና አስቀድሞ ትርጉም የተሰጠበትን በሰበር መ/ቁ 31891 የተሰጠውን ውሳኔ ማየት እንደሚቻለው ሁለቱም ለ12 ዓመታት ተለያይተው እንደኖሩ፣ ተጠሪም በውጭ ሀገር በመኖር ላይ እንዳለች ሌላ ባል አግብታ ትኖር እነደነበር በክርክር ደረጃ የቀረበው ሳይጣራ የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ለሰጠው ዳኝነት እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በደፈናው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም በሰጠባቸው "ሌሎች መዝገቦች" የሚለው አገላለጽ በሰበር መ/ቁ 14290፤20938 የተሰጠውን

ለመጥቀስ ፈልጐ ከሆነም ተለያይተው የኖሩ ተጋቢዎች በየፊናቸው የየራሳቸውን ህይወት ስለመጀመራቸው፣ ሟች ሌላ ሚስት አግብተው ስለመኖራቸው ተረጋግጦ መሆኑ ሁሉ ታይቶ ትርጉም የተሰጠበት ስለሆነ በፍሬ ነገር ረገድ በአሁኑ አመልካች በምንያ ገ/ስላሴ እና ተጠሪ ወ/ሪት መሰረት ዓለማየሁ መካከል ከተነሳው ክርክር ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ የሚመሳሰል ባለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 454/97 መሰረት ታይቶ ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እና የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ከማስረጃ አቀባበል ሥርዓትና ከአዋጅ ቁጥር 454/97 አፈጻጸም (ረገድ) አንጻር ሲታይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ 14194 በ26/2/2003 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ፤ በአ/አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14801 በ20/7/03 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1706/00 በቀን 6/11/2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፀንቷል፡፡

ይህ የሰበር ክርክር ስላስከተለው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 75562

ሰኔ 18 ቀን 2004 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ሶፊያ መሐመድ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ መሐመድ ይመር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ በተጠሪ ስም እጣ የደረሰው ቢሆንም ቅድመ ክፍያ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስ በኋላ የተከፈለበት ኮንዶሚኒየም ቤት የጋራ ነው ተብሎ የሥር ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሳኔ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በጻፉት የሰበር ማመልከቻ አከራካሪው የኮንዶሚኒየም ቤት በጋብቻ ጊዜ በስማቸው የደረሰ ቢሆንም እጣው ሊደርስ የቻለው መንግስት ለሴቶች የተለየ የእጣ እድል ስርዓት በመዘርጋቱ በመሆኑ እና እጣው ከደረሰ በኋላም ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈርሶ ለቤቱ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚሉትን የቅሬታ ነጥቦች ጠቅሰዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ተጠሪ የጋራ ንብረቶች ናቸው የሚሏቸውን አይነታቸውንና ብዛታቸውን በመግለፅ ዳኝነት መጠየቃቸውን የስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚከራከሩበት በሰሚት ሳይት የሚገኝ ሕንፃ ቁጥር 148/11 ባለ ሁለት መኝታ በተጠሪ ስም የተመዘገበ የኮንዶሚኒየም ቤት እጣው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ የወጣ በመሆኑ በትዳር ጊዜ የተፈራ የጋራ ንብረት ስለሆነ ልንካፈል ይገባል የሚል የዳኝነት ጥያቄ ይገኝበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11 ውስጥ በ350 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሰፈረና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት፣ የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መኖራቸውን ገልፀው ክፍፍሉ እንዲደረግ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ

አመልካች ለተጠሪ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በሰጡት መልስም በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 10/11 ውስጥ በ350 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሰፈረና በአመልካች ስም የተመዘገበ መኖሪያ ቤት የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መኖራቸውን ሳይክዱ ክፍፍሉ ቢደረግ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን የገለፁ ሲሆን የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ግን የጋራ ስላልሆነ ተጠሪ ሊጠይቁ አይችሉም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የንብረት ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱም ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ የኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ መሆኑን ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለቅድመ ክፍያ ከፈልኩ የሚሉትን የብር 32,048.40(ሰላሳ ሁለት ሺህ አርባ ስምንት ብር ከአርባ ሳንቲም) ግማሽ ብር 16,024.20(አስራ ስድስት ሺህ ሃያ አራት ብር ከሃያ ሳንቲም) ተጠሪ እንዲተኩላቸው፣ ቤቱ ከነቀሪው እዳው ግን የጋራ ነው፣ በማለትና የታመኑትን ንብረቶች በሕጉ አግባብ ሊከፋፈሉ የሚችሉበትን መንገድ በመዘርዘር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የኮንዶሚኒየም ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ሚያዚያ ወር 2002 ላይ አከራካሪው የኮንዶሚኒየም ቤት በተጠሪ ስም የደረሳቸው መሆኑን ፣ ሰኔ 02 ቀን 2002 ዓ.ም. ደግሞ ጋብቻቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረሱን፣ ከዚህም በኋላ የጋብቻ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር ባልተካሄደበት ሁኔታ ነሐሴ 17 ቀን 2002 ዓ.ም አመልካች ለኮንዶሚኒየም ቤቱ ቅድመ ክፍያ የከፈሉ መሆኑንና ጳጉሜ 04 ቀን 2002 ዓ.ም. ላይ ከሚመለከተው አስተዳደር አካል ጋር የኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ውል የተዋዋሉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ አመልካች አሁን በዚህ ሰበር ደረጃ

አጥብቀው የሚከራከሩት ቤቱ ሴት በመሆናቸው ባገኙት ልዩ ድጋፍ የደረሳቸውና ቅድመ ክፍያውንም ከጋብቻ መፍረስ በኋላ የከፈሉ በመሆኑ የጋራ ሊሆን አይችልም በሚል ምክንያት ነው፡ ፡ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ለእጣው እንዲመዘገቡ የተደረገው ተጠሪ ካላቸው የስራ ባህርይ አንፃር አመልካች በቋሚነት አዲስ አበባ ስለሚኖሩ ጉዳዩን ለመከታተል እንዲቻል ስለመሆኑና እጣውም ሴት በመሆናቸው በተለየ መንገድ ያላገኙት መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የቤተሰብ ሕጉን ያገናዘበ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በበላይ ፍርድ ቤት ሊነሳ እንደማይችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ይህ ሰበር ችሎት የሚመራው በ1958ቱ የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጋችን በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ችሎትም ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ በመሆኑም በበታች ፍርድ ቤቶች ያልተነሳ የፍሬ ነገር ክርክር በሰበር ችሎት የሚነሳበት አግባብ የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ በጋብቻ ውስጥ የደረሳቸው መሆኑን ሳይክዱ እጣው በሴትነታቸው የደረሳቸው መሆኑን ጠቅሰው ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት የላቸውም በማለት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የቤቱ ዕጣ በጋብቻ ውስጥ ግራ ቀኙ እያሉ የደረሰ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች እጣውን በሴትነት ያገኙት ነው በማለት እዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክር ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች እጣው የደረሰው በጋብቻ ውስጥ መሆኑን ሳይክዱ ለቤቱ ቅድመ ክፍያ ከጋብቻ መፍረስ በኋላ በስማቸው ወይም ከግል ገንዘባቸው መክፈላቸውና ዉሉንም ከአስተዳደሩ ጋር ማድረጋቸው በጋብቻ ጊዜ የደረሰውን እጣ ውጤቱን የሚቀይረው ሊሆን የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የለም፡፡ የኮንደሚኒየም ቤት ለህብረተሰቡ የሚሰጥበትን አግባብ የሚገዙ ሕጎችም ከምዝገባ ጀምሮ የተለያዩ ሂደቶች ያሉ ስለመሆኑ የሚያሳዩ ሲሆን በትዳር ውስጥ የሚገኙ ባልና ሚስት ለእጣው ሲመዘገቡ ሁለቱም ሊመዘገቡ እንደማይችሉ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም አንዱ ተጋቢ በጋብቻ ጊዜ ስሙ ከተመዘገበና እጣው ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ከደረሰ በቤቱ ላይ የሚገኘው መብትና ግዴታ የተጋቢዎች የጋራ ነው ከሚባል በስተቀር የቅድሚያ ክፍያ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ በአጭር ጊዜ ወይም ወዲያውኑ በመከፈሉና ዉሉም የተዋዋለው ተጋቢ የግል ንብረት ነው የሚባልበት ህጋዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የኮንዶሚኒየም ቤቱ የግሌ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስርዓቱ ጠብቆ ያልቀረበና ሕጋዊ መሰረት የሌለው ሆኖ ስለተገኘ ነው በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት

ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ በመ/ቁ. 24526 ሐምሌ 19 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 115416 በ12/03/2004 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የኮንደሚኒየም ቤቱ እጣ የደረሰው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ስለሆነና አመልካች ለቤቱ ቅድመ ክፍያ በመክፍል ውሉን ከአስተዳደር አካሉ አደረግሁ የሚሉት ጊዜ ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ከፈረሰ በአጭር ጊዜ ውስጥና የንብረት ክፍፍሉ ባለተደረገበት ሁኔታ በመሆኑ ቤቱን የአመልካች የግል ንብረት ነው ለማለት የሚያስቸል ሕጋዊ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣው ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳአውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት